1. ዌብሳይቶች ላይ በመመዝገብ ገንዘብ እንደሚሰራ ሰምተው ይሆናል አልተሳሳቱም። ለምሳሌ ያህል እንኳን ጉግል አድሴንስ በ2015 10 ቢሊዮን ዶላር ማስታወቂያዎቹን ለሚያሳዩ ድረ ገጾች ከፍሏል። ብዙ ኢትዮጵያዉያንም ኦንላይን በመስራት ቀላል የማይባል ገንዘብ ያገኛሉ-ምንም እንኳን ልምዱን የሚያካፍል ሰው ባናገኝም። በጣም ደስ የሚለው ደግሞ እነዚህ ገንዘብ የሚከፍሉ ድረ ገፆች ብዙዎቹ የሀዋላ አገልግሎት ስለሚጠቀሙ ገንዘብ ስለሚያገኙበት መንገድ አይጨነቁም።
2. ብዙ ህገወጥ ገንዘብ ማግኛ ድረ ገፆች ቢኖሩም እኛ የምናሳያችሁ ህጋዊ በሆነ መንገድ እንዴት ገንዘብ እንደሚያገኙ ነው። እባክዎ የመቆመሪያ እና የገንዘብ ምንዛሬ እንዲሰሩ የሚጋብዝ መልዕክት ቢደርስዎ አይቀበሉ። ህገወጥ ከመሆኑ በላይ ያልተገባ ኪሳራ ላይ እንደሚወድቁ አይጠራጠሩ።
3. ኮምፒውተር ከ ኢንተርኔት connection ጋር የግድ ያስፈልጋል።ቤትዎ ወይም ቢሮዎ የማያገኙ ከሆነ internet መጠቀም ይችላሉ። ብዙ ጊዜ ሊሸጡት የሚችሉት ተሰጥኦ ቢኖሮት ጥሩ ነው። ባይኖሮትም ግን game ስለተጫወቱ፣ app ስላወረዱ እና መጠይቅ ስለሞሉ ብቻ ገንዘብ የሚከፍሉ ስላሉ አይጨነቁ።
4. ጦማሩን ለሶስት ዋና ቦታዎች ከፍለነዋል። እነሱም “አገልግሎት በማቅረብ ገንዘብ ማግኘት”፣ “ማስታወቂያዎችን በማሳየት ገንዘብ ማግኘት” እና በነፃ ገንዘብ ማግኘት” ብለናቸዋል። የመጀመሪያዎቹ ክፍሎች ላይ የምናያቸው በሙሉ እንዴት አድርገው አገልግሎቶን በማቅረብ ገንዘብ እንደሚያገኙ ነው።
5. የመጀመሪያዎቹ ጦማሮች የሚያተኩሩት ላቀረቡት ስራ በሚከፍሉ ድረ ገፆች ላይ ነው። designer ከሆኑ(website፣ logo፣ graphic) ወይም ብሎግ የሚፅፉ ከሆኑ፤ ብቻ የትኛውንም ነገር መስራት የሚችሉት ካለ ለሽያጭ በማቅረብ ገንዘብ ስለሚያገኙበት መንገድ ነው። በጦማሮቹም ከ ድረ ገፆቹ ጋ ይተዋወቃሉ፣ sign up ያደርጋሉ፤ እንዴት ገንዘብ እንደሚሰሩ ይማራሉ፤ በስተመጨረሻም ገንዘቦትን እንዴት በአስተማማኝ መልኩ እንደሚያገኙ ይማራሉ! ብዙ የምናካፍሎት ስላለን ድረ ገፃችንን ይጎብኙ!